# ዳግም ጥምቀት

**(Re-baptism)**

ታሪካዊ አመጣጡ፣ የቤተክርስቲያን አባቶች ክርክር፣ የጉባኤያት ውሳኔ እና አሁን ላይ በኦረንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ያለው አቋም

---

ርዕሰ ጉዳይ **(Subject):** የቤተክርስቲያን ታሪክ እና ዶግማ


አቅራቢ **(Prepared by):** ኪዳነ ማርያም

## ማውጫ (Table of Contents Overview):


1. መግቢያ: የጥምቀት ትርጉም እና የክርክሩ መነሻ
2. የካታሪዎች እና የኖቫቲያን መነሳት
3. የቅርጣግና (የቅዱስ ቆጵርያኖስ) አቋም: "ከቤተክርስቲያን ውጪ ድኅነት የለም"
4. የሮም (የፓፓ እስጢፋኖስ) አቋም: የሥላሴ ስም እና የጥምቀት ህልውና
5. የምስራቁ ዓለም (የቅዱስ ፊርሚልያኖስ) ተቃውሞ
6. አስታራቂው ዲዮናስዮስ ዘእስክንድርያ
7. የቅዱስ አውግስጢኖስ መፍትሔ: የጥምቀት መኖር (Validity) እና ጸጋን ማስተላለፍ (Efficacy)
8. የቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሳርያ ቀኖናዊ ክፍፍል
9. የጉባኤያት ውሳኔዎች: ኒቅያ እና ቁስጥንጥንያ
10. አሁናዊ የኦሪንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት አቋም

# ዳግም ጥምቀት

ቤተክርስቲያን ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ እስካሁን ድረስ ከያዘቻቸው ዋነኛ ሥርአቶቿ መካከል ጥምቀት አንዱ ነው። ጥምቀት ለሌሎቹ ምሥጢራት መግቢያ በር ከመሆኑ ባሻገር የክርስትና ሕይወት መጀመሪያ ነውና ትልቅ ቦታ ተሰጥቶት የሚፈጸም ምሥጢር ነው። መጠመቅ ማለት ከእግዚአብሔር መወለድ ፣ ወደ ጌታ ቤተሰብም መግባት ነው ስለዚህም የማይጠፋ ማኅተምን በሰው ላይ ያስቀምጣል ስለዚህም ከማይደገሙ ምሥጢራት ተርታ ይመደባል። ከእናት እና ከአባት የምንወለደው አንዴ እንደሆነው ሁሉ ከውኃ እና ከመንፈስም የምንወለደው አንዴ ነው። አንድ ልጅ ለወላጆቹ ምንም ባይታዘዝ እንኳን ከልጅነት መብቱ ይፍቁታል እንጂ ከልጅነቱ ሊፍቁት አይችሉም አንዴ ወልደውታልና ከእግዚአብሔር የተወለደ ልጅም እንዲሁ ነው ልጅ ስለሆነ ወራሽ ነው ነገር ግን ለአባቱ ካልታዘዘ ወራሽነቱን ያጣል እንጂ ልጅነቱን አያጣውም ስለዚህ አንድ የተወለደ ልጅን ድጋሚ ማጥመቅ መንፈስ ቅዱስን እንደ መሳደብ ይቆጠራል። በዚህም ምክንያት ዳግም ጥምቀት በክርስቲያኖች ሁሉ ዘንድ የተወገዘ ነው ስለዚህም ኤፌ 4፡4 "አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት" ሲል ፤ የቁስጥንጥንያ ጉባኤ ደግሞ "ለኃጢአት ሥርየት በሚሆን በአንዲት ጥምቀት እናምናለን" ይላል ይህ ሁሉ የሚያሳየን ጥምቀት አንድ ብቻ መሆኑን ነው።

ዳግም ጥምቀት በሁሉም ዘንድ ኃጢአት መሆኑ ከታመነ ዘንድ በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ለምን የዳግም ጥምቀት ክርክር በተደጋጋሚ ይነሳል? ከ3ተኛው ክፍለ ዘመን ሰው ቆጵርያኖስ እስከ 16ተኛው ክፍለ ዘመን ዳግም አጥማቂዎች (አናባፕቲስት) ድረስ የዳግም አጥማቂነት ክስ ይቀርባል እነርሱ ግን ዳግም ማጥመቅ ኃጢአት መሆኑን ይቀበላሉ። ታድያ ክሱ ከየት መጣ? ብለን ስንጠይቅ መልሱ የሚሆነው አንድ ሰው በትክክል ተጠምቋል ለማለት መስፈርቱ ምንድነው? የሚለውን ጥያቄ በመመለስ ይገኛል። የትኞቹም ዳግም አጥማቂያን ተብለው ሚከሰሱ ቡድኖች እነርሱ ዳግም እያጠመቅን ነው ብለው አያምኑም ይልቅስ በትክክል ያልተጠመቀ ሰውን ለመጀመሪያ ጊዜ በትክክል እያጠመቅን ነው ይላሉ እንጂ ፤ አንድ ሰው በትክክል ካልተጠመቀ ደግሞ በውኃ ውስጥ አለፈ እንጂ በኢየሱስ ስም ክርስቲያናዊውን ጥምቀት ተጠመቀ አይባልም። ስለዚህ አንድ ሰው የመጀመሪያው ጥምቀት ትክክል አልነበረም በማለት ለሁለተኛ ጊዜ (በእርሱ አስተሳሰብ ለመጀመሪያ ጊዜ) አንድ ሰውን "የዳግም አጥማቂነትን" ኃጢአት ሳይሠራ ማጥመቅ ይችላል። ለምሳሌ ቅዱስ ጳውሎስ ሐዋ 19 ላይ በኤፌሶን ሲያልፍ ደቀመዛሙርትን ያገኛል እነዚህ ደቀ መዛሙርት አምነዋል ተጠምቀዋል ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን አልተቀበሉም የተጠመቁት የዮሐንስን ጥምቀት ነበ፤ ስለዚህም ጳውሎስ በኢየሱስ ስም አጥምቋቸው መንፈስ ቅዱስን ተቀብለዋል እነዚህ ሰዎች የኢየሱስ የሆነው ጥምቀት ለመጀመሪያ ጊዜ ተቀበሉ እንጂ ድጋሚ እየተጠመቁ አይደለም።

ይህ ጉዳይ በመጀመሪያዎቹ የቤተክርስቲያን ክፍለ ዘመናት ችግር አልፈጠረም ነበር የኢየሱስን ጥምቀት የሚፈጽሙ ክርስቲያኖች ብቻ ናቸውና። ነገር ግን በኋላ ላይ ከክርስቲያኖች መካከል መናፍቃን መነሣት ሲጀምሩ ችግር እየፈጠረ መጣ ፤ በተለይ ንጉሥ ዴስዮስ ካደረገው የክርስቲያኖች ስደት በኋላ በካታሪዎች መነሳት ግሎ ወጣ። የካታሪዎች መሥራች የሮሙ ኖቬቲያን ነው ፤ መሳደድን ፈርተው ከጥምቀት በኋላ እምነታቸውን የካዱ ክርስቲያኖች ቢጸጸቱ ቤተክርስቲያን ልትቀበላቸው አትችልም፤ ኃጢአታቸውንም ይቅር ማለት የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው ብሎ ተነሣ በሮምም ካለችዋ ቤተክርስቲያን ተለይቶ በራሱ ወጣ። የእኛ ዋና አላማ ስለካታሪዎች መናገር አይደለምና በዚህ እናብቃና ወደ ጉዳያችን እንመለስ። ካታሪዎች በዶግማ ከክርስቲያኖች ጋር ተመሳሳይ ነገር ነው ሚያምኑ ቢሆኑም ነገር ግን ከሃዲዎች ንስሐ የላቸውም ብለው ከቤተክርስቲያን ተለዩ ፤ ተለይተውም አዳዲስ ክርስቲያኖችን ማጥመቅ ጀመሩ እነዚህ በእነርሱ እጅ የተጠመቁ ሰዎች ግን ንስሐ ገብተው ወደ ቤተክርስቲያን ተመለሱ ሲመለሱ ቤተክርስቲያን እንዴት ትቀበላቸው? በዚህ ጉዳይ ሁለት አብያተ ክርስቲያናት ተለያዩ ሮም እና የሰሜን አፍሪካዋ ቅርጣግና።

## የቅርጣግና ቁርጥ አቋም

የሰሜን አፍሪካዋ ቅርጣግና ጳጳስ የነበረው ቆጵርያኖስ "***Salus Extra Ecclesiam Non Est*** _ ከቤተክርስቲያን ውጪ ድኅነት የለም" በሚለው አቋሙ የሚታወቅ ሲሆን በመናፍቃን የተጠመቁ ሰዎች ወደ ቤተክርስቲያን ሲመለሱ ቤተክርስቲያን እንዴት ትቀበላቸው በሚለው ላይ ቁርጠኛ አቋም ነበረው። ለእርሱ መናፍቃን የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ የላቸውም ስለዚህ የሌላቸውን ጸጋ ሊያስተላልፉ አይችሉም ስለዚህ የመናፍቃን ጥምቀት ውኃ ውስጥ ተነክሮ ከመውጣት ያለፈ ጥቅም የለውም ስለዚህም እነዚህ ሰዎች ወደ ቤተክርቲያን ሲመጡ ቤተክርስቲያን ድጋሚ ሳይሆን ለመጀመሪያ ጊዜ በትክክል ታጠምቃቸዋለች። ለምሳሌ በመልእክት 75 ላይ እንዲህ ይላል "መንፈስ ቅዱስ በመኃልየ መኃልይ፣ በክርስቶስ አምሳል እንዲህ ሲል ያውጃል፦ 'ርግብዬ፥ መደምደሚያዬ፥ አንዲት ናት፤ ለእናትዋ አንዲት ናት፥ ለወለደቻትም የተመረጠች ናት።' ... እንግዲህ፣ ዓለም በዚህ መንገድ በነጻበትና በጠራበት በዚያ ጥምቀት፣ በኖህ መርከብ ውስጥ ያልነበረ ሰው በውኃ መዳን ይችል ቢሆን ኖሮ፤ አሁንም ጥምቀት ለእርሷ ብቻ በተሰጣት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሌለ ሰው በጥምቀት ሕያው መሆን በቻለ ነበር።"[1] ስለዚህ ለቆጵርያኖስ ከመርከቡ ውጪ ያሉ ሰዎች ውኃው ለጥፋት እንጂ ለድኅነት እንዳልሆናቸው ሁሉ ከቤተክርስቲያን ውጪ ያለ ጥምቀትም እንዲሁ የጥፋት ቢሆን እንጂ ለድኅነት ሊሆን አይችልም።

እንዲሁም በመልእክት 69 ላይ እንዲህ ይላል "ደግሞስ ራሱ የሌለውን ማን ሊሰጥ ይችላል? ወይም ራሱ መንፈስ ቅዱስን ያጣ ሰው እንዴት መንፈሳዊ ተግባራትን ሊፈጽም ይችላል? ስለዚህ፣ 'እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ ይላል እግዚአብሔር' ተብሎ እንደ ተጻፈ፣ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጣው ያልተማረው ሰው በተቀደሱ ሰዎች በኩል በውስጡ እንዲቀደስ መጠመቅና መታደስ አለበት።"[2] በዚህ መልእክቱም ቆጵርያኖስ እንደሚነግረን መናፍቃን ከቤተክርስቲያን በመለየታቸው የሚቀድሰውን መንፈስ ቅዱስ አጥተውታል ስለዚህ በሌላቸው ቅድስና ሌላውን በጥምቀት ሊቀድሱ አይችሉም ስለዚህም ወደ ቤተክርስቲያን የሚመጡ ሰዎች ሁሉ በጥምቀት መቀደስ አለባቸው።

የቆጵርያኖስ ሙግት ከተጠማቂው ጋር ብቻ የተገናኘ አይደለም ይልቅስ ከውኃውም ጋር ጭምር ነው ፤ በሰሜን ኣፍሪካም ሆነ በእስክድርያ (ከእስክንድርያ ሥርዓትን የተቀበልን ኢትዮጵያውያንን ጨምሮ) ተጠማቂው ከመጠመቁ በፊት ውኃው ይባረካል ፣ ይቀደሳል የሚያጠምቅ የተቀደሰው ውኃም ይሆናል (እኛ ማየ ገቦ የምንለው) ተጠማቂውም በዚህ በተቀደሰ ውኃ ውስጥ ይጠመቃል እንጂ በማንኛውም ውኃ ውስጥ አይጠመቅም ስለዚህ የቆጵርያኖስ ሙግት አጥማቂው መናፍቅ ከሆነ ተጠማቂውን መቀደስ አይችልም ብቻ ሳይሆን ውኃውን ራሱ መቀደስ አይችልም የሚለው ላይ ይሆናል ፣ ውኃውን መቀደስ ካልቻለ ደግሞ ማጥመቅም አይችልም መልእክት 70 ላይ እንዲህ ይጽፋል "የሚጠመቀውን ሰው ኃጢአት በጥምቀቱ

---

[1] The Holy Spirit declares in the Song of Songs, saying, in the person of Christ, 'My dove, my undefiled, is one; she is the only one of her mother, she is the choice one of her that bare her.'... If, then, in that baptism of the world thus expiated and purified, he who was not in the Ark of Noah could be saved by water, he who is not in the Church to which alone baptism is granted, can also now be quickened by baptism." Epistle 75 by Cyprian of Carthage : https://www.newadvent.org/fathers/050675.htm

[2] "Who, moreover, can give what he himself has not? Or how can he discharge spiritual functions who himself has lost the Holy Spirit? And therefore he must be baptized and renewed who comes untrained to the Church, that he may be sanctified within by those who are holy, since it is written, 'Be holy, for I am holy, says the Lord.' Epistle 69 by Cyprian of Carthage : https://www.newadvent.org/fathers/050669.htm

አማካኝነት ማጠብ እንዲቻለው፣ ውኃው አስቀድሞ በካህኑ ሊነጻና ሊቀደስ ይገባል። ... ነገር ግን ራሱ ያልነጻና መንፈስ ቅዱስ በውስጡ የሌለበት ሰው እንዴት ውኃውን ሊያነጻና ሊቀደስ ይችላል?"[3]
የቆጵርያኖስ አቋም ሲጠቃለል ቤተክርስቲያን አንዲት ናት ፣ የምትፈጽመውም ጥምቀት አንድ ነው ፤ ከቤተክርስቲያን ውጪ ያሉ ሰዎች ግን ጥምቀትን መፈጸም አይችሉም የጥምቀት ባለቤት ከክርስቶስ የማጥመቅን ሃላፊነት የተቀበለች ቤተክርስቲያን ብቻ ናት ስለዚህ የመናፍቃን ጥምቀት ፣ ጥምቀት ሳይሆን ሻወር ነው ስለዚህ በቤተክርስቲያን ሳይጠመቅ በመናፍቃን ተጠምቆ የመጣ ሰው ምፍንቅናውን ከካደ ቤተክርስቲያን ልትቀበለው የሚገባው በጥምቀት ነው። እንዲሁም "ዳግም አጥማቂ" መባሉን በጥብቅ ይቃወማል ይልቅስ እያጠመኩት ያለሁት ለመጀመሪያ ጊዜ ነው በማለት ይሞግታል። የቆጵርያኖስ ሙግት ከዚህ የተነሣ ብቻ ሳይሆን ከትውፊትም ጭምር ነው ቅርጣግና ከቀድሞ ጀምሮ መናፍቃን ወደ ቤተክርስቲያን ሲመለሰ ታጠምቅ ነበር ስለዚህ አሁን በማጥመቃችን እንቀጥላለን ሲል በጥብቅ ይሞግታል።

## የሮም የላላ አቋም

ከቅርጣግና የሜድትራንያንን ባሕር ተሻግራ የምትገኘው ሮም በዳግም ጥምቀት ላይ ጠንከር ያለ አቋም ነበራት በሥላሴ ስም የተጠመቀ ሰውን ድጋሚ ማጥመቅ ምሥጢሩን እና መንፈስ ቅዱስን መሳደብ አድርጋ ነው ነው ምትወስደው። በ3ተኛው ክፍለ ዘመን የነበረው ፓፓ እስጢፋኖስ ቆጵርያኖስን አወግዝሃለሁ እስኪለው ነበር የተቃወመው ፤ የቆጵርያኖስ "ዳግም ጥምቀት" አስተምህሮ ሐዋርያዊ ትውፊት እንዳልሆነና ቆጵርያኖስ የፈጠረው አድርጎ አስቦ ነበርና።

ለእስጢፋኖስ አንድን ጥምቀት ትክክለኛ የሚያደርገው ጥምቀቱ የሚፈጸምበት የሥላሴ ስም እንጂ የአጥማቂው ሁኔታ አይደለም ስለዚህ አጥማቂው ምንም እንኳን መናፍቅ ቢሆን በሥላሴ ስም ጥምቀትን እስከፈጸመ ድረስ ጥምቀቱ ትክክለኛ ነው ስለዚህ ከምንፍቅናው ወደ ቤተክርስቲያን ሲመለስ ቤተክርስቲያን በሜሮን ወይም በንስሐ ብቻ ልትቀበለው ይገባል እንጂ ድጋሚ ልታጠምቀው አይገባም። የእስጢፋኖስ ጽሑፎች በጊዜ ሒደት ቢጠፉም ከሞጋቾቹ ቆጵርያኖስ እና ፊርሚልያኖስ ጽሑፎች ውስጥ አንዳንድ የእርሱን አመለካከት እናገኛለን ለምሳሌ ፊርሚሊያኖስ ለቆጵርያኖስ በላከለት መልእክት ላይ ለእስጢፋኖስ እንዲህ ይላል ""ነገር ግን እርሱ፥ 'የክርስቶስ ስም ለእምነትና ለጥምቀት ቅድስና እጅግ ጠቃሚ ነው፤ ስለዚህም ማንም ሰው በየትኛውም ስፍራ በክርስቶስ ስም ቢጠመቅ፥ ወዲያውኑ የክርስቶስን ጸጋ ያገኛል' ይላል"[4]።

ይህ አቋም የካቶሊክ ቤተክርስቲያን በኋላ ዶግማዋ የምታደርገውን "Ex Opere Operato"[5] አቋም የያዘ ነው ፤ ማለትም ምሥጢሩ የሚፈጸመው በፈጻሚው ብቁነት ሳይሆን በሥራው በራሱ ነው ሥራውን የሚሠራው ክርስቶስ እራሱ እንጂ ካህኑ አይደለም ስለዚህ ካህኑ ምንም ኃጢአተኛ ቢሆን ፣ መናፍቅም ቢሆን ሠሪው አንድ ነውና ከሥራው የተነሣ ብቻ ምሥጢሩ ይፈጸማል። ጥምቀት ላይም እንዲሁ የሥላሴ ስም

---

[3] "The water must first be cleansed and sanctified by the priest, that it may be able, by its baptism, to wash away the sins of the man who is baptized.... But how can he cleanse and sanctify the water who is himself unclean, and in whom the Holy Spirit is not?" Epistle 70 by Cyprian of Carthage : https://www.newadvent.org/fathers/050670.htm

[4] "But, says he, the name of Christ is of great advantage to faith and the sanctification of baptism; so that whosoever is anywhere so-ever baptized in the name of Christ, immediately obtains the grace of Christ." Epistle 74 of Firmilian to Cyprian : https://www.newadvent.org/fathers/050674.htm

[5] By The Work Worked.

በመጠራት ከተፈጸመ ስሙ ራሱ ኃይል አለውና ውኃውንም ለመቀደስ ሆነ ወደ ተጠማቂው ጸጋን ለማስተላለፍ በቂ ነው የሚል ሙግት ነው እስጢፋኖስ የያዘው።

ከዚህ በተጨማሪ እስጢፋኖስ የሱ አቋም ዓለም አቀፋዊ ከመሆኑ አንጻር ይሞግታል መናፍቃን እንኳን ከአንዱ ምንፍቅና ቡድን ወደ ሌላው ምንፍቅና ቡድን ሰው ሲሔድ እንደማያጠምቁት በመጠቆም በጥምቀት ጉዳይ የተለየ አቋም የያዙት እንደ ቆጵርያኖስ ብቻ መሆናቸውን በመያዝ ይሞግታል ፤ እዚሁ የፊርሚሊያኖስ መልእክት ላይ እንዲህ ይለናል "ደግሞም፥ እስጢፋኖስ በመልእክቱ ላይ፦ 'መናፍቃን ራሳቸው ሳይቀሩ በጥምቀት ጉዳይ አንድ ልብ ናቸው፤ እርስ በርሳቸውም ከአንዱ ወደ ሌላው የሚመጡትን አያጠምቁም' ብሎ ለተናገረው ክፍል በሚገባ መልሰሃል፤ ይህም እኛም እንዲሁ ማድረግ የሚገባን በማስመሰል ነው።"[6] ይሄ ሙግት ለእስጢፋኖስ በጥምቀት ጉዳይ ከነ ቆጵርያኖስ ውጪ ሁሉም ስምምነት እንዳላቸው የሚያሳይ ሲሆን ፤ ለቆጵርያኖስ ግን መናፍቃን ዱሮውንም ሁሌም ስህተት መሆናቸውን የሚያሳይ ነው የሆነበት።

እስጢፋኖስ ግን ይህን አቋሙን በመሞገት ብቻ ያበቃ አልነበረም ይልቅስ እርሱ የሮም ጳጳስ በመሆኑ የበላይ አድርጎ አስቧልና ቆጵርያኖስ እና የሰሜን አፍሪካ ጳጳሳት “ዳግም ጥምቀትን” የማያቆሙ ከሆነ እንደሚያወግዛቸውና ከቤተክርስቲያን አንድነት እንድሚለያቸው ዛተ። ለዚህ ምላሽም የሰሜን አፍሪካ ጳጳሳት በቆጵርያኖስ መሪነት በቅርጣግና ጉባኤ አድርገው “የጳጳሳት ጳጳስ የሚባል ጳጳስ የለም ጳጳሳት ሁሉ እኩል ናቸው ሊፈርዱብን የሚችለው አለቃ ክርስቶስ ብቻ ነው እንጂ የሮሙ ጳጳስ አይደለም፤ ስለዚህም በእኛ ትውፊት መሠረት መናፍቃን ወደ ቤተክርስቲያን ሲመለሱ እናጠምቃለን”[7] ብለው አወጁ። ይሄን ጊዜ ክርክሩ ወደ ቤተክርስቲያናት መወጋገዝ ደረጃ ስለደረሰ ወሬው ከምዕራቧ ቤተክርስቲያን አልፎ ወደ ምስራቅ ደረሰ ፤ የቀጰዶቅያዋ ቂሳርያ ጳጳስ የነበረው ፊርሚልያኖስ በኃይል ተነሣ።

## ፊርሚልያኖስ ዘቂሳርያ

ፊርሚሊያኖስ ለቆጵርያኖስ በላከው መልእክቱ ላይ እስጢፋኖስ ላይ ጠንካራ ትችት ሲሰነዝር ይታያል ፤ ትችቱን የሰነዘረው በዳግም ጥምቀት ላይ ባለው አቋም የተነሣ ብቻ አልነበረም ይልቅስ እራሱን “የጴጥሮስ መንበር” ላይ የተቀመጥኩ ነኝ በማለት የጴጥሮስን ስም ያሰድባል ሲበዛ ራሱን ከፍ ከፍ ያደርጋል “ማን ስለሆነ ነው እሱ አወግዛቹሃለሁ” የሚለው አይነት ትችት ያቀርብበታል። ለምሳሌ ለቆጵርያኖስ  በላከው መልእክቱ ላይ እንዲህ ይላል "ነገር ግን በእስጢፋኖስ የተደረጉት እነዚህ ነገሮች ለጊዜው ይቆዩን፤ የእርሱን ድፍረትና ትዕቢት በማሰብ፣ እርሱ በክፉት ከፈጸማቸው ነገሮች የተነሣ በራሳችን ላይ የበለጠ ዘላቂ ሐዘን እንዳናመጣ።"[8] ፊርሚሊያኖስ ፓፓው ያለ ሥልጣኑ መናፍቃንን በጥምቀት እንቀበላለን የሚሉትን ሁሉ አወግዛለሁ ማለቱን እንደ ታላቅ ድፍረት እና ትዕቢት ነው ያየው ስለዚህ እንዲህ እያለ ይቀልድበታል "ነገር ግን እስጢፋኖስ አሁን በድፍረት እንዳደረገው፣ በዚህ ምክንያት ከዓለም አቀፋዊት ቤተ ክርስቲያን ሰላምና

---

[6] "But, moreover, you have well answered that part where Stephen said in his letter that heretics themselves also are of one mind in respect of baptism; and that they do not baptize such as come to them from one another... as if we also ought to do this." Letter 74

[7] Council of Carthage of AD 256

[8] “But let these things which were done by Stephen be passed by for the present, lest, while we remember his audacity and pride, we bring a more lasting sadness on ourselves from the things that he has wickedly done.” Epistle 74

አንድነት መለየት ፈጽሞ አልነበረም፤ እርሱ ግን በእናንተ ላይ ሰላምን አፈረሰ... በዚህም ብፁዓን ሐዋርያት የሆኑትን የጴጥሮስንና የጳውሎስን ስም አጎደፈ።"[9]

ለፊርሚልያኖስ የሥላሴ ስም ሰውየው ምፍቅና ውስጥ እንኳን ቢሆን ጸጋን የሚያስተላልፍ "አስማት"[10] አይደለም ጸጋም ከእውነት ተለይቶ ሊኖር አይችልም። መናፍቃን ግማሽ እውነት ብቻ ስላላቸው በጥምቀትም ሙሉ ክርስቶስን ሊሰጡ አይችሉም ይልቅስ የተከፈለ ክርስቶስ ነው ያላቸው ፤ ክርስቶስ ግን አንድ ነው፣ ክርስቶስንም በምልዓት ያላት ቤተክርስቲያን ብቻ ናት ስለዚህም ትክክለኛውን ጥምቀት ማጥመቅ የምትችለው ቤተክርስቲያን ብቻ ናት። በዚሁ መልእክት ላይ እንዲህ ሲል ይሞግታል "በዚህ ሁኔታ የቤተ ክርስቲያንን ታላላቅና ሰማያዊ ስጦታዎች ለመናፍቃን አሳልፎ የሚሰጥ ሰው፥ ይህን ያህል ጸጋ እንዳላቸው አጥብቆ ለሚከራከርላቸው ለእነርሱ፣ ከእነርሱ ጋር ኅብረት ከመፍጠር በቀር ሌላ ምን እያደረገ ነው?"[11] ፤ ፊርሚልያኖስ እዚህ ላይ ፓፓውን በምንፍቅና እየከሰሰው እንደሆነ አስተውሉ የመናፍቃን ጥምቀት ጸጋ ያስተላልፋል እያለ በጥብቅ የሚከራከርላቸው ከሆነ ምናልባት ከእነሩሱ ጋር ኅብረት ቢፈልግ ነው እያለ ከባድ የሆነ ክስን ያመጣበታል ፤ ስለዚህ መናፍቅ ነው ፣ መናፍቅ ነህ የሚለው ክስ ከሁለት አብያተ ክርስቲያናት አልፎ ሮም ከሰሜን አፍሪካና ምስራቅ ጋር ወደ መሆን እየሔደ ይመስላል ፤ ሮም በጴጥሮስ ሥልጣን ወስኛለሁ ትላለች ሌሎቹም በጉባኤ ወስኛለሁ ይላሉ ነገሩ የቤተክርስቲያንን የመከፈል አደጋ ሊያመጣ ይመስላል እንግዲህ ይሄኔ ነው የእስክድርያ ጳጳስ ዲዮናስዮስ ወደ ታሪኩ የገባው።

ፓፓ ዲዮናስዮስ ዘእስክድንርያ

ዲዮናስዮስ ለሰሜን አፍሪካዋ ቅርጣግና በቅርበት በምትገኘው የግብጿ እስክድርያ ጳጳስ በመሆኑ ጉዳዩን በቅርበት ያውቀዋል በአስተምህሮ ወደ እነ ቆጵርያኖስ የተጠጋ ቢሆንም ግን በቤተክርስቲያን ሰላም እንዲመጣ ይፈልግ ነበርና ለማስማማት ወደ መጣር ነበር የገባው። በዚህ ጊዜ እስጢፋኖስ ለማውገዝ እያስፈራራ ሲሆን ፣ ፊርሚሊያኖስ ደግሞ እስጢፋኖስን "ከሀዲ ይሁዳ" እያለው ነው። [12]

ዲዮናስዮስ ሰላም ይመጣ ዘንድ ለእስጢፋኖስ እንዲሁም ለእስጢፋኖስ ተከታይ ፓፓ ሲክስተስ እንዲህ ሲል መልእክት መጻፉን የታሪክ ጸሐፊው አውሳብዮስ ዘቂሳርያ ይዘግብልናል "ስለዚህ ጉዳይ እርሱ [ፓፓ እስጢፋኖስ] አስቀድሞ ስለ ሄለነስ እና ፊርሚልያኖስ፣ እንዲሁም በኪልቅያ፣ በቀጰዶቅያ፣ በገላትያ እና በአጎራባች ሀገራት ስላሉት ሁሉ ጽፎ ነበር፤ ይኸውም 'መናፍቃንን ዳግም ያጠምቃሉ' በሚል ምክንያት ከእነርሱ ጋር ኅብረት እንደማያደርግ በመግለጽ ነው።

---

[9] "And yet on this account there is no departure at all from the peace and unity of the Catholic Church, such as Stephen has now dared to make; breaking the peace against you... even herein defaming Peter and Paul the blessed apostles." Ibid

[10] አስማት ግዕዝ ሲሆን ስሞች ማለት ነው የአጋንንትን ስምች በመጥራት የሚፈጸም ተአምራዊ ነገር ለማመልከት ይውላል ለፊርሚልያኖስም የመናፍቃን ጥምቀት የሥላሴ ስም ስለተጠራ ጸጋ ያስተላልፋል ማለት ስም በመጥራት የሚፈጸም አስማት ያደርገዋል የሚል ሙግት ነው ያለው።

[11] "He who concedes and gives up to heretics in this way the great and heavenly gifts of the Church, what else does he do but communicate with them for whom he maintains and claims so much grace?" Ibid

[12] እዚህ ጋር ያሳቀኝን ነገር note ላስገባ ብዬ ነው ፊርሚልያኖስ ገራሚ ሰው ነው ፓፓው "የጴጥሮስ መንበር" ላይ ተቀምጭያለሁ ቢል የት ይሰማል "አንተ የጴጥሮስ አሰዳቢ ደፋር ይሁዳ" እያለ ይመልሳል እንጂ። እነ ቆጵርያኖስ ምንም እንኳን የፓፓውን ሥልጣን ቢቃወሙም ለሮም ክብር ነበራቸውና polite ሆነው ነበር ሚመልሱት ፤ ፊርሚሊያኖስ ግን ፓፓው "የጴጥሮስን ሥልጣን አለኝ" ቢል እንኳን "ከነ ሥልጣንህ ገደል ግባ" የሚለው ይመስላል።

ነገር ግን እስቲ የነገሩን ክብደት አስተውል። እኔ [ዲዮናስዮስ] እንደተረዳሁት፣ በታላላቅ የጳጳሳት ጉባኤዎች ላይ [በ230 ዓ.ም. በኢቆንዮን፣ በቅርቡ በተደረገው የሰሜን አፍሪካ ሲኖዶስ፣ ወዘተ] ስለዚህ ጉዳይ እንዲህ የሚል ውሳኔ ተላልፏልና፤ ይኸውም ከምንፍቅና የሚመለሱ ሰዎች አስቀድመው ትምህርት ሊማሩ፣ ከዚያም ከአሮጌው እና ርኩስ ከሆነው እርሾ ቆሻሻ ታጥበው ሊነጹ ይገባቸዋል የሚል ነው። እኔም ስለዚህ ሁሉ ነገር እየለመንኩት ጻፍኩለት።"[13]

ዲዮናስዮስ በመጨረሻም እስጢፋኖስ አወግዛለሁ የሚለውን ነገር ከሔደበት ቤተክርስቲያንን እንደሚከፍል በማስጠንቀቅ በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ጉዳይ ጣልቃ እንዳይገባ ነገር ግን በሮም የፈለገውን እንዲያደርግ ይመክረዋል። ስለዚህ የዲዮናስዮስ መፍትሔ ሮም እንደ ሮም ትሁን ፣ ቅርጣግና እንደ ቅርጣግና ትሁን፣ ቂሳርያም እንደ ቂሳርያ ትሁን ቤተክርስቲያን ግን አትከፈል የሚል ይመስላል።

በመጨረሻ ግን ጉዳዩ የተፈታው በስምምነት ሳይሆን በሰማዕትነት ነበር ፤ በ257 ዓ.ም ንጉሠ ነገሥት ቫሌርያኖስ ክርስቲያኖች እንዲሳደዱ እና እንዲገደሉ ትዕዛዝን አወጣ በዚህም ፤ ፓፓ እስጢፋኖስ በ257 ዐረፈ ፤ ቆጵርያኖስ በ258 አንገቱን ተቀልቶ ሰማዕትነትን ተቀበለ ፤ ፓፓ ዲዮናስዮስ ደግሞ ከመንበሩ ተሳደደ። በዚህ ሁኔታም 3ተኛው ክፍለ ዘመን ችግር አስነሥቶ ችግሩን ግን ሳይፈታ ለቀጣዩ ትውልድ አስተላለፈ። በኋላም ችግሩን ለመፍታት " De Rebaptismate-በእንተ ዳግም ጥምቀት" የተባለው ጸሐፊው የማይታወቅ ጽሑፍ ሙግት ላይ በመመሥረት ቅዱስ አውግስጢኖስ እና ከምሥራቁ የቅዱስ ባስልዮስ ሙግት ላይ በመመሥረት በቁስጥንጥያ ጉባኤ ላይ ውሳኔ ያገኛል ፤ በዚህ ውስጥ ግን የኒቅያ ጉባኤም ተጠቃሽ ነው።

አውግስጢኖስ ዘኤጶን

ቅዱስ አውግስጢኖስ የጻፈበት ዘመን ዶናታውያን የሚባሉ መናፍቃን ከቅርጣግና የተነሡበት ዘመን ነው። ዶናታውያን የቆጵርያኖስን አቋም ወደ ጫፍ በመውሰድ አጥማቂው ካህን መናፍቅ ብቻ ስለሆነ ሳይሆን የመንፈስ ፍሬ የሌለው ኃጢአተኛ እንኳን ቢሆን ምሥጢራትን መፈጸም አይችልም ፣ ጸጋንም ማስተላለፍ አይችልም በማለት በዶናተስ መሪነት ከቤተክርስቲያን የወጡ ሰዎች ናቸው። አውግስጢኖስ ለእነርሱ ምላሽ ይሰጥ ዘንድ "Ex Opere Operato" እና " Ex Opere Operantis[14]" የሚባሉትን አቋሞች ለይቶ ያስቀምጣል። Ex Opere Operato ማለት ከላይ እንዳብራራነው ምሥጢራቱ ጸጋን የሚያስተላልፉት በምሥጢር ፈጻሚው ሰው ላይ በመመሥረት ሳይሆን እራሱ ስለሥራው ጸጋን ያስተላልፋሉ ማለት ነው። Ex Opere Operantis ማለት ደግሞ ምሥጢራት የሚፈጸሙት ስለሥራው ብቻ ሳይሆን ስለሠሪውም ጭምር ነው ማለት ነው ፤ ሠሪው መናፍቅ ፣ ኃጢአተኛ ፣ ከሀዲ ወዘተ ከሆነ ትክክለኛ ምሥጢርን መፈጸም አይችልም ማለት ነው።

በተለይ ጥምቀትን ስንመለከት ደግሞ ቅዱስ አውግስጢኖስ "De Rebaptismate" በተባለው ጽሑፍ ላይ በመሥረት Ex opere operatoን ለጥምቀት ያውለዋል ፤ ነገር ግን ከፓፓ እስጢፋኖስ በመለየት የመናፍቃን ጥምቀት ጸጋን አያስተላልፍም ይላል። ይህ እንዴት ይሆናል? ጥምቀት በትክክል ለመፈጸም

---

[13] "He [Pope Stephen] therefore had written previously concerning Helenus and Firmilianus, and all those in Cilicia and Cappadocia and Galatia and the neighboring nations, saying that he would not commune with them for this same cause; namely, that they re-baptized heretics. But consider the importance of the matter. For truly in the largest synods of the bishops [Iconium in approx 230 AD, the recent North African synod, etc], as I [Dinoysus] learn, decrees have been passed on this subject, that those coming over from heresies should be instructed, and then should be washed and cleansed from the filth of the old and impure leaven. And I wrote entreating him concerning all these things."Book VII, Chapter 5 of Ecclesiastical History

[14] By The Work of the Worker

በፈጻሚው ላይ የማይመሠረት ከሆነ እንዴት ጸጋ አያስተላልፍም? ተብሎ ሲጠየቅ አውግስጢኖስ የጥምቀትን ተፈጻሚነት በሁለት ጎራ ይከፍለዋል ፤ በትክክል መፈጽሙ (Validity) እና ጸጋን ማስተላለፉ (Efficacy) በማለት። መናፍቃን በትክክል ጥምቀትን መፈጸም ስለመቻላቸው በእንተ ጥምቀት በተባለ ጽሑፉ እንዲህ ይላል "የክርስቶስ ጥምቀት በመናፍቃን ዘንድ ቢሰጥ ወይም ቢቀበሉት፥ በመናፍቃን ጠማማነት የተነሣ ሊሻር አይችልም።"[15] ነገር ግን ጸጋንም እንደማያስተላልፍ ይልቅስ ጸጋው የሚሰጣቸው ወደ ቤተክርስቲያን ተመልሰው በሜሮን ሲታተሙ መሆን እንዲህ በማለት ይጽፋል "እኛ 'በዶናታውያን ዘንድ ጥምቀት እንዳለ' እናረጋግጣለን፣ ይህም 'በእነርሱ ዘንድ እርግጥ ነው፣ በእኛም ዘንድ የታመነ ነው'፤ ነገር ግን 'በእነርሱ ዘንድ ጥምቀቱ በአግባቡ (በትክክል) እንደማይቀበሉት' እንሞግታለን። ስለዚህም 'የክርስቶስ ጥምቀት ከውጭ ቢቀበሉት እንኳን፥ ጠቃሚ የሚሆነው በእርሷ [በዓለማቀፋዊት ቤተክርስቲያን] ውስጥ ብቻ ስለሆነ'፣ አንድ ሰው 'በዶናታውያን ዘንድ በመጠመቁ ያለው መተማመን ጥቅመ ቢስ (ትርፍ የለሽ) ነው።'[16]

የአውግስጢኖስ ሙግት በአጭሩ ሲጠቀለል ከቤተክርስቲያን ውጪ ጥምቀት ፣ መናፍቃንም የሚያጠምቁት ጥምቀትም በሥላሴ ስም እስከሆነ ድረስ ትክክለኛ ነው ወደ ቤተክርስቲያን ሲመለሱ መደገም የለበትም በትክክል ተጠምቀዋልና ነገር ግን በጥምቀት የሚገኘውን ጸጋ ከቤተክርስቲያን ውጪ ሆነው በጥምቀቱ በኩል ሊያገኙት አይችሉም ምክንያቱም ከቤተክርስቲያን የመለየት ኃጢአታቸው ጸጋውን እንዳያገኙ ይገድባቸዋልና ልክ ወደ ቤተክርስቲያን አንድነት ወደ ቅዱሳንም ኅብረት በመጡ ጊዜ ግን ወደ ክርስቶስ አካልነት እጅን በመጫን በሜሮን ሲታተሙ ከቤተክርስቲያን የመለየት ኃጢአታቸው ይወገዳል ጸጋውን እንዳያገኙ የገደባቸው የመለየት ኃጢአቱ በመሆኑ እርሱ እንቅፋት ሲነሳ የጥምቀቱ ጸጋ ወደ እነርሱ ይፈሳል ተጠቃሚም ይሆኑበታል ፤ ስለዚህ ከቤተክርስቲያን ውጪ ጥምቀት አለ ነገር ግን ጥምቀት ከቤተክርስቲያን ውጪ ጥቅም የለውም ነገር ግን ጥምቀቱ የጎደለ ሆኖ ሳይሆን የመለየት ኃጢአት ጸጋን እንዳያስተላልፍ ስለገደበው ነው። De Rebaptismate የተሰኘው ጽሑፍ ለዚህ ምሳሌ የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 8 ላይ ያለውን ታሪክ ይጠቅሳል ፤ ዲያቆኑ ፊሊጶስ የሰማርያ ሰዎችን ቢያጠምቃቸውም እርሱ ሐዋርያ ባለመሆኑ እጁን ጭኖ በመንፈስ ቅዱስ ማተም አልቻለም ነበር ስለዚህ እኒህ ሰዎች በትክክል ቢጠመቁም ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ገና አላገኙም ነበር ፤ ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ያገኙት ጴጥሮስ እና ዮሐንስ መጥተው እጃቸውን በመጫን በመንፈስ ቅዱስ ካተሟቸው በኋላ ነበር።

ባስልዮስ ዘቂሳርያ

ወደ ምስራቁ ዓለም ስንሔድ ደግሞ በፊርሚልያኖስ መንበር ቂሳርያ ላይ የተቀመጠው ታላቁ ቅዱስ ባስልዮስ ልክ እንደ ፊርሚሊያኖስ በግሉ መናፍቃን ወደ ቤተክርስቲያን ሲመጡ እንዲጠመቁ ቢፈልግም በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ግን Ekonomia የተባለውን መርህ ይከተላል። በመልእክት 188 ላይ ከቤተክርስቲያን የተለዩትን ሰዎች በ3 ይከፍላቸዋል መናፍቃን (heretics)፣ ተገንጣዮች (Schismatics) እና ሕገ ወጥ ማኅበሮች (unlawful congregations) በማለት። እንዲህ ሲል ይጽፋል "መናፍቃን ስንል ከትክክለኛው እምነት ጋር በተያያዘ ፈጽሞ የተቆረጡትንና የራቁትን ሰዎች ማለታችን ነው፤ ተገንጣዮች ስንል ደግሞ ስለ አንዳንድ

---

[15] "The baptism of Christ cannot be invalidated even by the perversity of heretics, when it is given or received among them." Augustine: On Baptism against Donatists , Book V Chapter 3: https://www.newadvent.org/fathers/14085.htm

[16] "We affirm... that baptism exists among the Donatists... [which] is asserted by them and allowed by us," yet we maintain "that with them it is not rightly received." Consequently, "his confidence in being baptized among the Donatists is somewhat profitless," because "the baptism of Christ is only profitable in it [the Catholic Church], even when it has been received elsewhere." Augustine: On Baptism against Donatists , Book I Chapter 3: https://www.newadvent.org/fathers/14081.htm

የቤተ ክርስቲያን ጉዳዮች እና በጋራ መፍትሔ ሊገኝላቸው በሚችሉ ጥያቄዎች ምክንያት የተለዩትን ሰዎች ነው፤ «ሕገ ወጥ ማኅበራት ስንል ደግሞ ሥርዓት በጎደላቸው ቀሳውስት ወይም ኤጲስ ቆጶሳት፣ አልያም ትምህርቱ በሌላቸው ምእመናን የተደረጉ ስብስቦችን ማለታችን ነው።"[17] መናፍቃን የሚላቸውን ሲጠቅስ "ሚኒኪያውያን ፣ ቫሌንቲኖሳውያን ፣ መርቅዮሳውያንን" ሲጠቅስ እነዚህ ውስጥ የተጠመቁ ሰዎች ወደ ቤተክርስቲያን ሲመጡ መጠመቅ አለባቸው የመናፍቃን ጥምቀት ተቀባይነት የለውምና። ተገንጣዮችናን እና ሕገ ወጥ ማኅበሮችን ግን በንስሐ መቀበል እንችላለን ከቤተክርስቲያን ፈጽመው አልተለዩምና በማለት ይሞግታል።

## የጉባኤያት ውሳኔዎች

### የ314 አርለስ ጉባኤ

የአርለስ ጉባኤ በምዕራቡ ዓለም ማንኛውም ጥምቀት በአብ ፣ ወልድ ፣ መንፈስ ቅዱስ ስም እስከተፈጸመ ድረስ ትክክለኛ መሆኑን ያወጀ ጉባኤ ነበር ቀኖና 8 ላይ እንዲህ ይላል "ዳግም በማጥመቅ የራሳቸውን ልዩ ሕግ ስለሚከተሉት ስለ አፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት የተወሰነው ይህ ነው፦ ማንኛውም መናፍቅ ወደ ቤተ ክርስቲያን ቢመጣ፣ ስለ እምነቱ (ስለ ሃይማኖት ጸሎት) ይጠየቅ፤ በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስም ስም እንደተጠመቀ ከተቆጠረ፣ እጅ መጫንን ብቻ ይቀበል።"[18]

### የኒቅያ ጉባኤ

የኒቅያ ጉባኤ በሁለት መናፍቃን አይነቶች ላይ ውሳኔን አሳልፏል እነርሱም ኖቫታውያን (መጀመሪያ ላይ ያነሳናቸው ካታሪ) እና ጳውሎሳውያን (ሥላሴ አንድ አካል ነው የሚሉ የጳውሎስ ሳምሳጢ ተከታዮች)። ጉባኤው ኖቫታውያን ድጋሚ ሳይጠመቁ እጅን በመጫን ብቻ መቀበል እንደሚገባ በቀኖና 8 ላይ እንዲህ ይላል "ካታሪ የተባሉት ወደ ቤተ ክርስቲያን ቢመጡ… በዚያው [በክህነት] መዓረጋቸው ይቀጥሉ… እጅ መጫንንም ብቻ ይቀበሉ ።" [19] ጳውሎሳውያን የተባሉት መናፍቃን ግን ዳግም መጠመቅ እንዳለባቸው በቀኖና 19 ላይ እንዲህ ይላል "ወደ ዓለም አቀፋዊት ቤተ ክርስቲያን የሚመጡ ጳውሎሳውያን፣ በሁሉም መንገድ እንደገና እንዲጠመቁ ተደንግጓል።"[20]

የኒቅያ ጉባኤ በዚህ ውሳኔው ሚያሳየን ለጥምቀቱ ትክክለኝነት የሥላሴ አስተምህሮ አስፈላጊ መሆኑን ነው ካታሪዎች ምንም ከቤተክርስቲያን ቢለዩ ትክክለኛውን ትምህርተ ሥላሴ ነበራቸው ፣ ጳውሎሳውያን ግን በአንድ አካል አምላክ ስም ስለሚያጠምቁ ጥምቀታቸው ተቀባይነት አላገኘም።

### የቁስጥንጥንያ ጉባኤ

የቁስጥንጥንያ ጉባኤ ቀኖና 5 ከተለያዩ ምንፍቅና ቡድኖች የሚመጡትን ሰዎች ቤተክርስቲያን እንዴት መቀበል እንዳለባት አቅጣጫን ያስቀምጣል ፤ አርዮሳውያን ፣ መቅዶንዮሳውያን ፣ ሰባታውያን ፣ ኖቫታውያን (ካታሪ) ፣ ቴትራዳውያን ወዘተ የመሰሉትን መናፍቃን ፣ ምንፍቅናቸውን ካወገዙ በኋላ በሜሮን በመታተም ቤተክርስቲያን ትቀበላቸዋለች ፤ ነገር ግን አንድ ጊዜ ብቻ ብቅ ጥልቅ (በአንድ አምላክ አብ ስም) በማለት የሚጠመቁ አውናምዮሳውያን ፣ በአብ ፣ በወልድ ፣ በሞንታነስ ስም የሚጠመቁ ሞንታኖሳውያን (ሞንታነስ

---

[17] Basil the Great : Letter 188 : https://www.newadvent.org/fathers/3202188.htm#:~:text=Even%20a%20fool%2C%20it%20is,letter%20from%20your%20industrious%20self.

[18] Council of Arles AD 314 , canon 8 : https://www.fourthcentury.com/arles-314-letter-to-sylvester/

[19] Council of Nicaea AD 325 , Canon 8: https://www.newadvent.org/fathers/3801.htm

[20] Council of Nicaea AD 325, Canon 19 : https://www.newadvent.org/fathers/3801.htm

መንፈስ ቅዱስ ነው ስለሚሉ) ፣ አብ እና ወልድን አንድ የሚያደርጉ ሰባልዮሳውያን እንደገና መጠመቅ አለባቸው በማለት ውሳኔን አስተላልፏል።[21]

## አሁናዊ የኦሬንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት አቋም

ስድስቱ የኦሬንታል አብያተ ክርስቲያናት ስለ "ዳግም ጥምቀት" አሁን ላይ የያዙትን አቋም እንዴት ያዙ? የሚለውን ታሪካዊ ዳራ እንዳፍ ብንል ሌላ ለብቻው ትልቅ ጥናት ይፈልጋል ነገር ግን አሁን ላይ አብያተ ክርስቲያናቱ የያዙትን አቋም ብቻ እናስቀምጥ። እኒህ አብያተ ክርስቲያናት ስድስት ቢሆኑም ወደ 3 ሥርዓት (Rite) ልንከፍላቸው እንችላለን እነርሱም ፡ እስክንድርያዊ ፣ ምዕራብ ሶርያዊ እና ፣ አርመንያዊ ናቸው። በእስክንድርያዊ ስር የሚካተቱት ፡ የግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ፣ የኤርትራ ኦርቶዶክሳዊ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ናቸው ፤ በምዕራብ ሶርያዊ ስር የሚካተቱት ደግሞ ፤ የሶርያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን እና የሕንድ ማላንካራ ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያን ናቸው ፤ በመጨረሻው በአርመንያዊ ስር ደግሞ የሚካተቱት ፣ አርመንያዊት ሐዋርያዊት ቤተክርስቲያን የኤችሚያድስ መንበር እና የኪልቅያ መንበር ናቸው።

ከሦስቱ ሥርዓት አሁን ላይ ቆጵርያኖሳዊ ሃሳብን የያዘው እስክንድርያዊ ሥርዓት ነው ፤ 3ቱ አብያተ ክርስቲያናት ሁናዊ ሁኔታቸው የትኛውም የምናፍቃን ጥምቀት ጥቅም አልባ እንሆነና የትኛውም ሰው ወደ ቤተክርስቲያን ሲመጣ መጠመቅ እንዳለበት ያስተምራሉ። ለምሳሌ አቡነ ሺኖዳ ሳልሳዊ ይህን ጥብቅ አቋማቸውን በኤፌሶን 4:4 ላይ ይመሠርቱታል "አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት" ስለሚል መጀመሪያ በሃይማኖት አንድ ሳንሆን በጥምቀት አንድ ልንሆን አንችልም በሃይማኖት አንድ ከሆንን በኋላ ግን በጥምቀት አንድ ልንሆን እንችላለን ሲሉ ይሞግታሉ።

ነገር ግን ከአቡነ ሺኖዳ በኋላ በማርቆስ መንበር ላይ የተቀምጡት የአሁኑ አቡነ ታዋድሮስ በ2017 ከካቶሊክ ቤተክርስቲያን ጋር በጥምቀት በጋራ ተስማምተው ነበር አንዱ ወደ አንዱ ሲሔድ እንዳይጠመቅ [22] ነገር ግን የቅብጥ ቤተክርስቲያን ሲኖዶስ ወድያው ነበር እርምጃ የወሰደው ፓፓውም ተቃውሞ የገጠማቸው ብዙ ጳጳሳት በፓፓቸው እንደተከዱ ነበር ያሰቡት ስለዚህም ስምምነቱ በሲኖዶስ ደረጃ ሳይጸና ቀረ። የእስንድርያ ቤተክርስቲያን ልጆች የሆኑት የኢትዮጵያ እና የኤርትራ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናትም እንዲሁ ጥብቁን ቆጵርያኖሳዊ አቋም እንደያዙ ነው።

ወደ ሶርያ እና ሕንድ አብያተ ክርስቲያናት ስንሔድ ደግሞ በተቃራኒው እስጢፋኖሳዊ አቋምን የያዙ ይመስላል በተለይ ከሌሎቹ ኬልቄዶናዊ አብያተ ክርስቲያናት አማኞችን ሲቀበሉ ድጋሚ አያጠምቁም ይልቅስ በቅዳሴ ላይ በሚፈጸም ምሥክርነት ይቀበባሉ እንጂ።[23]

የአርመን ሐዋርያዊት ቤተክርስቲያንን ስንመለከት ደግሞ ሰዎችን በሁለት መንገድ ትቀበላለች ካቶሊክ እና ኢስተርን ኦርቶዶክስን በንስሐ ብቻ ስትቀበል ፕሮቴስታንቶች በሥላሴ ስም እስከተጠመቁ ድረስ በሜሮን በማተም ትቀበባለች። [24]

---

[21] Council of Constantinople AD 381 Canon 5 : https://www.newadvent.org/fathers/3808.htm

[22] 2017 Common Declaration
[23] The 1984 Joint Declaration with the Catholic Church.
[24] https://stjohnarmenianchurch.com/sacraments

በመጨረሻም ስንጠቀልለው በ3ተኛው ክፍለ ዘመን በቆጵርያኖስ እና በእስጢፋኖስ መካከል የተፈጠረው ቅራኔ አሁንም ድረስ በ21ደኛው ክፍለ ዘመን በኦሬንታል አብያተ ክርስቲያናት መካከል የቀጠለ ይመስላል እንግዲህ ወደፊት በእነዚህ መካከል የዓለም አቀፍ ጉባኤ ቢደረግ ይህ ጉዳይ መፍትሔ ያገኛል ብለን ተስፋ እናደርጋለን ፤ ነገር ግን የቤተክርስቲያን ታሪክ እንደሚያሳየን ቀላል አድርገን የምናስበው ነገር ሁሉ ቀላል አለመሆኑን ነው ክርስቶስ ታሪክን ይዋጅ!

# ዋቢ መጻሕፍት (Works Cited)


**I. የቤተክርስቲያን አባቶች ጽሑፎች (Primary Sources - Church Fathers)**

- **Saint Augustine of Hippo.** *On Baptism, Against the Donatists*. Book I & Book V. (Translated by J.R. King). From Nicene and Post-Nicene Fathers, First Series, Vol. 4.
- **Saint Basil the Great.** *Letter 188 (The First Canonical Epistle).* (Translated by Blomfield Jackson). From Nicene and Post-Nicene Fathers, Second Series, Vol. 8.
- **Saint Cyprian of Carthage.** *Epistle 69: To Magnus.* (Translated by Robert Ernest Wallis). From Ante-Nicene Fathers, Vol. 5.
- **Saint Cyprian of Carthage.** *Epistle 70: To Januarius and Other Numidian Bishops.* (Translated by Robert Ernest Wallis). From Ante-Nicene Fathers, Vol. 5.
- **Saint Cyprian of Carthage.** *Epistle 75: To Magnus.* (Translated by Robert Ernest Wallis). From Ante-Nicene Fathers, Vol. 5.
- **Saint Firmilian of Caesarea.** *Epistle 74: To Cyprian.* (Translated by Robert Ernest Wallis). From Ante-Nicene Fathers, Vol. 5.
- **Eusebius of Caesarea.** *Ecclesiastical History.* Book VII, Chapter 5.

**II. የቤተክርስቲያን ጉባኤያት ቀኖናዎች (Canons of Church Councils)**

- **Council of Arles (314 AD).** *Canon 8.*
- **First Council of Nicaea (325 AD).** *Canon 8 (On the Cathari/Novatians)* and *Canon 19 (On the Paulianists).*
- **First Council of Constantinople (381 AD).** *Canon 5.*

**III. ዘመናዊ መግለጫዎች እና ሰነዶች (Modern Declarations & Documents)**

- **Common Declaration of Pope Francis and Pope Tawadros II.** (Cairo, Egypt, 2017).
- **Common Declaration of Pope John Paul II and Syrian Patriarch Zakka I Iwas.** (1984).
- St. John Armenian Church. *Sacraments: Baptism and Chrismation.* (Source for Armenian Apostolic Church practice).